አንደኛ ዓመት ቁጥር 4

1st Year No 4

ሐረር ግንቦት 4 ቀን 1988

Harar, May 12 1996


# የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
# ሐረር ነጋሪ ጋዜጣ
# HARAR NEGARI GAZETA
# HARARI PEOPLE NATIONAL REGIONAL STATE



| ያንዱ ዋጋ 1.00 | በሐረሪ ሕዝብ ክልል ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | የፖስታ ሣጥን ቁጥር 272 |
|---|---|---|



## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 4/ 1988

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኦዲት ጽቤት ማቋቋሚያ


አዋጅ ቁጥር 4/ 1988 .................................................... ገጽ 26


## የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኦዲት ጽ/ቤት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት የተጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የተመደበላቸውን መደበኛ በጀትና ካፒታል በጀት የሚያንቀሳቅሱ በመሆኑ፣ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ገቢዎችን የሚሰበስቡ በመሆኑ፣ የወጪ አወጣጣቸው ፣የገቢ አሰባሰባቸው፣ የሂሳብ አያያዝና አጠቃቀማቸው መመሪያ፣ ደንብና ሕግ የተከተለና ትክክለኛ መሆኑን መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

ይህንንም የሚከታተልና የሚያጣራ የኦዲት ጽህፈት ቤት ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ የሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መ/26/1/ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ምዕራፍ አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኦዲት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 4/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም እንዲሰጠው፣ ካላስፈለገ በስተቀር በዚህ አዋጅ

1 " ክልል" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልል ነው፤

2. "ምክር ቤት" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ነው፤

3. "የክልሉ መንግሥት" ማለት የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፤

4. "አስፈፃሚ አካላት" ማለት የክልሉ ምክር ቤት የሚያወጣውን ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሣኔዎች ለማስፈፀም የተቋቋሙ ቢሮዎች፣ ጽህፈት ቤቶችና ኮሚሽኖች፣ እንዲሁም የመስተዳድሩ ጽህፈት ቤት ናቸው፤

5. "ጽህፈት ቤት" ማለት የኦዲት ጽህፈት ቤት ነው፤

6. "ኃላፊ" ማለት የኦዲት ጽህፈት ቤት ዋና ኃላፊ ነው።

3. መቋቋም

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኦዲት ጽህፈት ቤት /ከዚህ በኃላ "ኦዲት ጽህፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

## ምዕራፍ ሁለት

4. የክልሉ መንግሥት ኦዲት ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኦዲትጽህፈት ቤት የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

1. የክልሉን ምክርቤት ጽህፈትቤት እና ማናቸውም የክልሉ መንግሥት ኃላፊነት ሥር የሚገኙ መሥሪያ ቤቶችን፣ የድርጅቶችና የማህበራትን ሂሳብ ይመረምራል፣ ያስመረምራል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1 በተመለከተው መሠረት ያከናወነውን የምርመራ ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለሚመለከተው የክልሉ መንግሥት የበላይ አካል ወይም ለመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፣
3. አንድ ሂሳብ ተንኮል በተሞላበትና ታማኝነት በጎደለው ሁኔታ መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህን ሂሳብ በሚመለከቱ መዛግብት፣ ሰነዶች፣ መዝከሮችና ሌሎች መሰል መረጃዎች ላይ ያሽጋል፣
4. በክልሉ ውስጥ በግል የሚሠሩ ኦዲተሮችና የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለመሰማራት መቻላቸውን የሚያረጋግጥ የምሥክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ይሰርዛል፣ የምስክር ወረቀት ሲሰጥና ሲያድስ የክልሉ መንግሥት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ተገቢውን ክፍያ ያስከፍላል፣
5. የተካሄዱ የሂሳብ ምርመራዎችን ይዘት በመመርመር የችግሮችን መንስዔ ወይም ምንጭ ያጠናል፣ እንዲሁም የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፣
6. የሂሳብና የንብረት ምርመራ ሥርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎች ያወጣል፤
7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር አስፈላጊ መስሎ ሲያገኘው ለውስጥ ኦዲተሮች ሥልጠና ይሰጣል፤
8. የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ስለ ገንዘብና የሂሳብ አጠባበቅ በሚያዘጋጀው ደንብ ላይ አስተያየት ናየሂሳብ ሙያ እንዲዳብር አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፤
9. ስለ አከናወነው ምርመራና የምርመራ ግኝቶች ለክልሉ ምክር ቤትና ለፌዴራሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት አጠቃላይ ሪፖርት ያቀርባል።

## ምዕራፍ ሦስት

### የክልሉ መንግሥት ኦዲት ጽህፈት ቤት ኃላፊ ተጠሪነትና ሥልጣንና ተግባር

5. የኃላፊው ተጠሪነት

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኦዲት ጽ/ቤት ኃላፊ ተጠሪነቱ ለክልሉ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

6. የኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኦዲት ጽ/ቤት ኃላፊ፡-

1. ጽህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ይወክላል፣
2. ለጽህፈት ቤቱ የተፈቀደውን በጀት በፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሠረት ያስተዳድራል፤
3. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ4 መሠረት ለጽህፈት ቤቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በበላይነት ያከናውናል።

## ምዕራፍ አራት

### ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

7. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች፤ ደንቦችና መመሪያዎች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም።

8. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በሐረር ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ሐረር ግንቦት 4ቀን 1988

አብዱላሂ እድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዚዳንት